REGION KRONOBERG

**ያደባ የሳንባ ነቀርሳ፥ ለበሽተኛ የሚሰጥ መረጃ (2016-09-19)**
**የቅድሚያ መከላከል ህክምና በማይሰጥበት ወቅት።**
*የተላላፊ በሽታ ሐኪሞች፥ የተላላፊ በሽታ መከላከያ ልሳን።*

**ኣንድ ሰው በሽታው እንዴት ይተላለፍበታል?**
የሳንባ ነቀርሳ ባክቴሪያ ከአንድ ሰው ወደ ሌላ የሚዛመተው በዓየር ውስጥ ነው። ይህ የሚሆነው በበሽታው የተለከፈውና ማጋባት የሚችል ሰው ሲስልና፥ በቅርቡ የሚገኝ ሰው ባክቴሪያውን በትንፋሹ ሲስብ ነው።

**ያደባ ሳንባ ነቀርሳ ምንድን ነው?**
ነቀርሳው የተላለፈባቸው ሰዎች ሁሉ አይታመሙም። የብዙ ሰዎች ተፈጥሯዊ የበሽታ መከላከያ ኃይል ባክቴሪያው እንዳያድግና እንዳይሰራጭ ሊገታው ይችላል። በዚህ መልኩ ባክቲሬያው ሰውነት ውስጥ እያለ ኣድብቶ ይቀመጣል። በዚህ ሁኔታ የሚገኘው ነው **ያደባ ሳንባ ነቀርሳ** የሚባለው።

**ያደባ ሳንባ ነቀርሳ በሽታ ኣይደለም**
ከደም ምርመራ (IGRA-Test) ወይም ከቆዳ ምርመራ (Tuberkulintest) በኋላ ያደባ ሳንባ ነቀርሳ ኣለብዎት ከተባሉ **ሙሉ በሙሉ ጤነኛ** ነዎት ማለት ይቻላል። እናም በሽታውን ወደ ሌላ ሰው ማጋባት ኣይችሉም። ይሁን እንጂ በሕይወት እስካሉ ድረስ በሽታው ኣንድ ቀን ሊከሰት ይችላል የሚል ስጋት ይኖራል፥ ሆኖም ይህ የሚያጋጥምበት ዕድል በጣም የመነመነ ስለሆነ ኣብዛኛዎቹ ያደባ ሳንባ ነቀርሳ ያለባቸው ሰዎች ህክምና ኣይደረግላቸውም።

**በኣንዳንድ ሁኔታ የቅድመ መከላከል ህክምና ሊሰጥ ይችላል**
ኣንዳንድ ሰዎች ላይ በሽታው ኋላ ሊከሰትባቸው ይችላል የሚል ስጋት በእጅጉ ካለ የቅድመ መከላከል ህክምና እንዲያደርጉ ይጋበዛሉ። ይህ ህክምና የሚደረግው በቅድሚያ ለህፃናትና ለታዳጊዎች ሲሆን ከእርግዝናና ከወሊድ ጋር በተያያዘ ምክንያትም ይሰጣል። በተጨማሪም የተፈጥሮ በሽታ የመከላከል ኃይላቸው የተዳከመባቸው ለምሳሌ፥ የካንሰር ህክምና የሚያደርጉ፥ ኢንሱሊን የሚወስዱ የስኳር በሽተኞች፥ ከባድ የኩላሊት ችግር ያለባቸው ሰዎችም ይደረግላቸዋል። የቅድመ መከላከል ህክምና ኣንዳንድ ጊዜ በቅርቡ የሳንባ ነቀርሳ ለያዛቸው ሰዎችም ይደረጋል።

**ሐኪምን ማነጋገር**
ወደፊት ዘለገ ያለ ሳል (ከሶስት ሳምንታት በላይ)፥ በመኝታ ግዜ በላብ መዘፈቅ፥ ትኩሳትና ያልታሰበ የክብደት መቀነስ ከታየቦት የሳንባ ነቀርሳ ምርመራ ለማድረግ ሐኪሞን ያነጋግሩ። እርጉዝ፥ ወይም ኢንሱሊን የሚወስዱ የስኳር በሽተኛ ከሆኑ፥ ከባድ የኩላሊት ችግር ካለብዎት የካንሰር ህክምና የሚያደርጉ ከሆነ፥ ወይም በሌላ ምክንያት የተፈጥሮ በሽታ የመከላከል ኃይልዎ ከተዳከመም ሐኪምዎን ከማነጋገር ወደ ኋላ ኣይበሉ። እነዚህ ሁኔታዎች በሚከሰቱበት ጊዜ የሳንባ ነቀርሳ ሊጠቁ ያለው ዕድል ከፍተኛ ነውና።


***smittskyddsenheten***
Centrallasarettet, 351 85 Växjö. ☎0470-588278